# የአቶ አበባው መህሪ(የመኢአድ ሊቀመንበር የነበሩ) ማንነት ሲፈተሸ

በቂም ተፀንሶ በበቀል ያደገ ወያኔ ኢሕአዴግ እንደ ሕዝብ በአማራ እንደ ሐገር በኢትዮጵያ ላይ ያነጣጠረው የወያኔ ኢሕአዴግ የዘረኝነት ፖሊሲ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ አበባው መሐሪ ሐምሌ 14 እና 15 ቀን 2005ዓም በተካሄደው በ3ኛ መ/ጠ/ጉባኤ ከተመረጡ በኋላ ከ18 የሥራ አስፈፃሚዎች ውሥጥ 14ቱን ጥላሸት በመቀባት፤ በማሣሣር እና በማባረር በምትካቸው በጠቅላላ ጉባኤው ከተሰጠው ኃላፊነት እና ከምርጫ ቦርድ እውቅና ውጭ የወያኔ የደህንነት አባሎችን በመተካት ለጥቂት ወራቶች ቢቆዩም አቶ አበባው መሐሪ የተመረጡበት ሂደት ለምርጫ ቦርድ በትክክል መረጃዎችን ባለማቅረባቸው ህጋዊነቱ እውቅና ስላላገኙ ሌላ የመኢአድ አሥቸኳይ መደበኛ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በኢ/ር ኃይሉ ሻውል አማካኝነት በ28-30/2/2007ዓም ተካሂዶ አዲስ አመራር ተመትርቶ ሥራቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ።
የአቶ አበባው መሐሪ ቅድመ ታሪክ እና ሥብዕናን ስናስታውስ በ3ኛ መ.ጠ.ጉባኤ እንደተናገሩት ለመኢአድ አባል የሆኑት በ1986 ዓም መሆኑን ቢገልፁም ከእሳቸው በሥተቀር በሌላ ወገን ለማረጋገጥ አልተቻለም ይልቁንም በአቶ ኢሣያስ አፈወርቅ እና በአቶ ታምራት ላይኔ አቀነባባሪነት አማራ ሻቢያን ይቅርታ እንዲጠይቅ በተቋቋመው ኰሚቴ ውስጥ ዋና አቀነባባሪ ከነበሩት በዋነኛነት የሚወሱ እና አፍራሽነታቸው ጎልቶ የሚወሳ መሆናቸው የታሪክ ማህደራቸው ያመላክታል። ከእሳቸው ጋር የነበሩ የእርቁ ሸማግሌዎች ውሥጥ፡-

1.አቶ ታደሠ ይመር(በ2002ዓም ሀገር አቀፍ ምርጫ ምርጫው ትክክል እና ታማኝነት ያለው መሆኑን የገለፁ)
2. አቶ መህሪ ዮሐንስ(በህይዎት የሌሉ በወቅቱ ቀባሪ ያጡ)
3.አቶ ዮሴፍ ለይኩን(በሕይዎት የሌሉ)
4.አቶ አበባው መሐሪ /የመኢአድ ሊቀ መንበር የነበሩ እና የወያኔ ጉዳይ እሥፈፃሚ/ እና ሌሎችም ይገኙበታል።
ወደ መኢአድ በመጡበት ወቅት የተሠጣቸውን ኃላፊነት የአንድነት አፍራሽ ተልኳቸውን አጠናክረው ለመወጣት ሞክረዋል።
በ3ኛ ጠ.መ.ጉባኤ ለአባላት እንደተናገሩት ከ1986 ዓም ጀምሮ ከ10 አመታት ባላነሰ በተባበሩት መንግሥታት በወርልድ ባንክ ውሥጥ በአፍሪካ በየትኛውም ሀገር ተዘዋውረው እርዳታ አድራሽ ሆነው ሲሰሩ እንደነበር ለአባላት ሲናገሩ ቆም ብለን ካሠብን የተቃዋሚ ፓርፒ አባል ይቅርና ከፖለቲካ ነፃ የሆነ እንኳንስ በወርልድ ባንክ በቀበሌ መዋቅር ሥራ ማግኘት የሚከብደው እንዴት ይህን ኃላፊነት ተሰጣቸው ብለን ራሳችንን ብንጠይቅ መልሱ መኢአድን ለማጥፋት መኢአድን መስሎ መገኘት መሆኑን ማረጋገጥ አይከብድም።
ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ልዕዋላዊነት ከሆዳቸው በስተቀር ህልምም ትልምም የሌላቸው አቶ አበባው መሐሪ በመኢአድ ላይ የፈፀሙት መጠነ-ሰፊ እና የማያባራ በደል፡-

1. አማራ ሻቢያን ይቅርታ እንዲጠይቅ በተቋቋመው የአስታራቂ ኰሚቴ ስብስብ ውስጥ ተካቶ ራሱን ሰድቦ ያሠደበን
2. በ2002 ዓም በተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችንን በተለይ በምስራቅ ጎጃም ማስጨፍጨፋቸው እና ማሳሰራቸው በተጨማሪ መኢአድ የአማራ ድርጅት ነው በማለት ብዙ ወረቀቶችን በተለያዩ ክልሎች በትነው አሥበትነዋል
3. ታህሳስ 2003 ዓም በተካሄደው የመኢአድ 2ኛ ጠ.መ.ጉባኤ እሳቸው በችሎታ እና በአቅም ማነስ ምክንያት ያልተካተቱት በነ ወ/ሪት መሶበ ቅጣው ሰብሣቢነት የካቲት 23ቀን 2003 ዓም መፈንቅለ-መኢአድ በማካሄድ በፓቲው አመራር እና አባላት መካከል ያለመተማመን ፋይል ከፍተው ሐምሌ 30 ቀን 2003 ዓም በተካሄደው አሥቸኳይ የማዕከላዊ ም/ቤት ስብሰባ በአመራሮች ድክመት አቶ አበባውን የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣውን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ካስቀመጡ በኋላ ፓርቲውን ከማፈራረስ በስተቀር የታየ ሀገራዊ የፖለቲካ ለውጥ አልታየም።
4. ራሳቸውን ከመዋቅር በላይ በማድረግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ወደጎን በመተው በውጭ ሀገር ለሚገኙ የፓርቲው የድጋፍ ማህበር የፓርቲው የአስተዳደር እና የፋይናንስ ኃላፊነኝ በማለት ከተለያዩ አለማት በስማቸው ገንዘብ ይሰበስቡ እንደነበር በካናዳ የሚገኘው የድጋፍ ማህበር በ25/03/2004 ዓም የፃፉት ደብዳቤ ያመላክታል።
5.በህዳር 2005 ዓም አካባቢ በመኢአድ ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ቁማ የነበረችውን የፐ/ር አስራት ወ/የስ መኪና ከጽ/ቤቱ ዕውቅና ውጭ ያለምንም ጫረታ ከአስተዳደርና ፋይናንሥ ሀላፊ ጋር በመሆን ሸጠው ለግል ጥቅማቸው አውለዋል።
6.ምርጫ ቦርድ በኦዲት ሪፓርት ሰበብ የፓርቲውን ጽ/ቤት ለመዝጋት በተሯሯጡበት ወቅት ጽ/ቤቱ የሒሳብ ባለሙያ ለመቅጠር በተንቀሳቀሰበት ወቅት የወያኔ የደህንነት አባላትን አስገብቶ ለማሰራት ሲሞክሩ በአቶ ተስፋዬ ታሪኩ ሲከሸፍባቸው ይህ ቤት አይረባም የሚል አሉባልታ ያሰሙ ነበር።
7. ሐምሌ 14 እና 15/2005 ዓም በተካሄደው 3ኛ ጠ/መ/ጉባዔ አቶ አበባው በሊቀመንበርነት ብቅ ካሉ በኋላ ባልተለመደ መልኩ ፓርቲውን በፍጥነት ማፈራረስና እውቅና ማሳጣት ጀመሩ
7.1 ከስራ አስፈፃሚ እውቅና ውጭ መንቀሳቀስ እና መዋቅራዊ አካሄድ አለመከተል፤
7.2 አመራርን እና አባላትን መከፋፈልና ጥላሸት መቀባት
7.3 ፓርቲያችንን ያለዕቅድ መምራት
7.4 የድጋፍ ማህበራትን መከፋፈል
7.5 አመራርን እና አባላትን ማሣሰር በተለይ አቶ ተሥፋዬ ታሪኩን(የመኢአድ ዋና ፀሐፊ የነበሩ እስከ አሁን ድረስ በሕይዎት መኖራቸው እና የት እንደታሰሩ አይታወቅም) ማሳሰራቸውን ማረጋገጫዎች በመጀመሪያ 01/03/06 ዓም የአዲስ አበባ አባላት

በተገኙበት አቶ  ተሥፋዬ ፓርቲውን እንደማይጠቅም ከተናገሩ በኋላ ከዚህ በኋላ በአንድ እጀ ጥይት በአንድ እጀ እስክርቢቶ ይዠ መዋጋት አልችልም ብለዋል በማስቀጠል 28/07/06 ዓም አባላት በተገኙበት ተሥፋዬ ታሪኩን ያባረርሁት ወጣቶችን እየመለመለ ወደ ሰሜን ስለሚልክ ነው ብለው የውሸት ናዳ ሳያፍሩ አውርተው በመስሎቻቸው አስወሩ በምጨረሻም በ28/02/07 ዓም ለሰሜን ቀጠና አባላት አቶ ተሥፋዬ ታሪኩ ጠቅላላ ጉባዔው ላይ እንደማይገኝ ከተገኘ አበባው አትበሉኝ ብለው የነበረ መሆኑን የሰሜን ቀጠና ም/ኃላፊ የሆኑት አቶ ዘመነ ምህረቴ ለጉባዔው አረጋግጠዋል
7.6 የፓርቲውን አደረጃጀትና ጥንካሬ ማዳከምና ማፈራረስ

፨በ25/02/06 ዓም በጀርመን ድምፅ ራድዮ ባደረጉት ቃለምልልስ አዘጋጁ ከዚህ በፊት እናንተ የህብረ ብሄር ፓርቲ ነበራችሁ አሁን ከብሄር ፓርቲዎች ጋር ትብብር መፍጠራችሁ የአቋም ለውጥነው ወይስ ምንድን ነው ተብለው ሲጠየቁ ሲመልሱ "ድሮ እኮ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዶ ነበር"ብለው የእነ ፕ/ር አስራትን ትግል ጥላሸት መቀባት፤

፨ ወደ አረብ ሀገር የተሰደዱ ወገኖቻችን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ በሚደረገው ርብርቦሽ ላይ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲ ምን ይላሉ ተብለው ሲጠየቁ "እዛው ሥራ ይስጧቸው" ብለው እርፍ! ከህልውና በፊት ሥራ ብለው ቀለዱብን

፨ በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ ከተመረጡት ሥራ አስፈፃሚዎች መካከል ከ18ቱ 14ቱን በማባረር በምትካቸው ከሥራ አሥፈፃሚ እና ከማዕከላዊ ም/ቤት አባላት ዕውቅና ውጭ የተመረጡ የወያኔ የደህንነት አባላትን በመተካት ጭራሽ የፓርቲውን ፌስ ቡክ በደህንነቶች ማስከፈት
፨የሕግና ሥነ-ስርዓት ኮምቴን በወያኔ ደህንነቶች በመሙላት በተለይም የህግና ሥነስርዓት ኮምቴ ፀሀፊ እና የፓርቲው አደራጅ የሆኑት አቶ ሙሉጌታ አበበ የባሌ ዞን መኢአድ ጽ/ቤት ኃላፊ ከመሆናቸው በፊት የወንድማቸውን ልጅ ደፍረው ወደ ወህኒ ከተወረወሩ በኋላ በአቶ አባይ ፀሀየ በሚመራው ደህንነት ክፍል አማካኝነት ተፈቶ ለመኢአድ የባሌ ዞን ሰብሳቢ እና በባሌ ሀገረ ስብከት ውሥጥ በሰባኪነት እንዲሰሩ ተደርገዋል በዚህ ወቅት አቶ በረከት ሥምዖን ተቃዋሚዎች የሚሰበስቧቸው አባላት በደም የተጨማለቁ ናቸው ብለው በየሚድያው መናገራቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ነገር ግን ይህንን ግለሠብ የፓርቲው አባላት በየጊዜው ከህላፊነት እንዲነሳ ተቃውም ሲያሰሙ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል ጽ/ቤት እንዳይደርስ አድርገውት የነበር ቢሆንም አቶ አበባው ወደ ኃላፊነት ሲመጡ በአማካሪነት ይዘውት ሲመጡ በአያሌው ተቃውሞ ደርሶበታል አቶ አበባው ግን እኩይ ተልኳቸውን ለመፈፅም እና ለማስፈፀም እስከ አሁን ድረስ በአፋራሽነት ይዘውት እየተጓዙ ናቸው።

፨ሌላው የአቶ አበባው የቅርብ አማካሪ የሆነው አቶ መላኩ መሠለ ቀደም ሲል የአየር ኃይል ራዳር ቴክኒሻን ነበርሁ የሚለው በካሳንችስ ስውር መንግስት ከእነ አቶ ተስፋ ማርያም እና ፍስሃ ዘሪሁን  መኢአድን ለማፈራረስ በተዘጋጀው ክንፍ ውስጥ በዋናነት የተመደበውና በ1997 ምርጫ በኋላ የቅንጅት እመራሮች ወደ ወህኒ ከተወረወሩ በኋላ በተለይ የመኢአድን አባላት እና አመራርን እያሣደዱ በማፈናቀልሥራ ላይ ተጠምዶ የነበረ መሆኑን በተለይ በምሥራቅ ጎጃም በጎንቻ ወረዳ ያሉ አባሎቻችን በጠቅላላ ጉባዔ ወቅት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።ይህ ግለሰብ አቶ አበባው ወደሥልጣን ሲመጡ አቶ መላኩ መሰለን ያለቅድመ ሁኔታ የአዲስ አበባ መኢአድ ጽ/ቤት ኃላፊ እና አደራጅ በማድረግ ሌሎች አፍራሽ ተልዕኮ ያላቸውን ፀረ-መኢአድ አቋም ያላቸውን በመያዝ በጠንካራ አመራሮች እና አባላት ላይ የማባረር የማሳሰር የማስገደል ተግባራትን አስፈፅመዋል።

፨ፓርቲው ከሚያውቀው አካውንት ውጭ በመክፈት ከድጋፍ ማህበር ገንዘብ የሰበሰቡ መሆኑን ከለንደን የድጋፍ ማህበር የተላከ ብር ለጠቅላላ ጉባዔው በአባላት የተገለፀ መሆኑን
፨ወቅታዊ መግለጫዋች ሰላማዊ ሰልፍ አለማድረግ እና የወያኔ ሀሰተኛ ፕሮፖጋንዳ አለመተቸት ለገዥው ፓርቲ አጋርነታቸውን ከመግለጽ ያነሰ ትርጉም የለውም
8. ከጥቅምት28-30/07 ዓም አስቸኳይ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በኋላ በፓርቲው ላይ የፈፀሙት በደልና ለወያኔ አጋርነትን የገለፁበት
8.1 በጠቅላ ጉባኤው ፊት ድክመታቸውን ከተቀበሉ በኋላ ስልጣናቸውን ያስረከቡ እና ከዚህ በኋላ በተራ አባልነት ብቻ የሚቀጥሉ መሆኑ የፃፉት ማመልከቻ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል ከአቶ አበባው መሐሪ ተቀብለው መድረኩን በሚመሩ አባላት ተነቦ ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተቀብሎታል። ይህን ባሉበት ማግሥት የፓርቲውን ዶክመንቶች፤ላፕ ቶፖች እና ማህተም ሰርቀው በመውሰድ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው፤
8.2 በፓርቲው አካውንት የነበረውን ብር 40 ሽ ብር እና 60ሽ ብር ከኢ/ር ኃይሉ ሻውል ለአባላት እንዲከፈል የሰጡትን ብር በድምሩ 100ሽ ብር ወስደው ለግል ጥቅማቸው አውለዋል
8.3 ከኢ/ር ኃይሉ ለፓርቲው የተስጠው መጽሐፍን ከስቶር በአጋሮቻቸው አዘርፈው የቻሉትን ወስደው ያልቻሉትን ቀደው የጣሉት መሆኑን በ30/02/07 ዓም የጉባኤው አባላት ተመልክተዋል
8.4 ጠቅላላ ጉባዔው በተካሄደበት ወቅት በአደራጆች ክፍል የተሸለሙትን የብአዴን ዋንጫና የብአዴንን ባንዲራ ምገኘቱን በወቅቱ ለጉባኤው ለእይታ ቀርቧል
8.5 በየካ ክ/ከ የደህንነት ከፍተኛ አካልና የየካ ክ/ከ ፖሉስ አዛዥ በሆኑት ኢንስፔክተር ብሩክ አማካኝነት በ07/03/07ዓም በእየሩስአለም ሆቴል ለጋዜጠኞች ፀረ-መኢአድ አቋም የሰጡት አቶ አበባው መሀሪ ህግና ደንብ የተላለፉ መሆናቸውን እና ሆቴሉንም በምን አግባብ እንደተፈቀደላቸው ሆቴሉንም የምንከስ መሆኑን በአካል የፓርቲው አመራሮች ሲጠይቋቸው ሆቴሉን

ያከራየናቸው በኢንስፔክተሩ ትዕዛዝ ነው ማለታቸውን አመራሮች ለህዝብ ይፋ አድርገዋል።
8.6 የጽ/ቤቱን ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ስላልሆኑ የቢሮየዕለት ተዕለት ስራ ለመስራት እማኞች ባሉበት ቢሮው ሲከፈት ድሮወራቸው ውስጥ የአቶ መለስ ዜናዊ ከ150 በላይ የቁልፍ መያዣ ስቲከሮች ተገኝቶ ለአባላት ለእይታ ቀርቦ በእዝግቢትነት ተቀምጧል።
8.7 በተለያዩ በወያንኔ የኢህአዴግ ደጋፊ ሚድያዎች በተለይ አውስታራሊያ የሚገኘው sbs እንደተናገሩት ኢ/ር ኃይሉ ሻውል በመጀመሪያ ቅንጅትን አፈረሱ በ2002 መኢአድን አዋረዱ አሁን ደግሞ የመኢአድን አባላት ከፋፈሉ እያሉ መሰረተ ቢስ አሉባልታ ከማሰርራጨታቸውም በላይ በፓልቶክ ከተለያዩ diaspora discussion classes ..... ህሊና አልባ ዲስኩራቸውን እያስተጋቡ ይገ&#0;ኛሉ።

ስለዚህ አቶ አበባው መሀሪ መኢአድን ለማጥፋት መኢአድን መስው የገቡ ህሊና አልባ ባንዳ ናቸው። የዚህ ዓይነት ስራዎችን በመሥራት የሚታወቀው አቶ አበባው ለዚህ ሥራው በሞጆ ከተማ ውስጥ "ሐርቨስት ኃ.የተ.የግ.ማህበር" የሚል የዶሮ እና የአሳማ እርባታ ያላቸው ሲሆን በ2006 ዓም ያለምንም ጫራታ ከ850ሽ ዶሮዎች ለኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ መሸጣቸው ይታወሳል ።ይህንና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ተደምሮ በግንቦት ወር 2006 ዓም በአካውንታቸው ከ48 ሚሊዮን ብር በላይ ማስገባታቸው የአይን እማኞች ይናገራሉ፣